ጥኅተ ሰማይ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወቅድስት አርሴማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንድነት ገዳም በካሊፎርንያ

# ሥርዓተ ገዳም

## መግቢያ

ይህ ገዳም ከዚህ ዓለም ከሚገኘው ምኞት ከሥጋዊ ብዕልና ክብር ተለይቶ እግዚአብሔርን በሥነ ፍጥረቱ እያሰቡ ከወዳጅና ከዘመድ ርቆ በርዕይና በሰሚዕ ከሚነሳው ፍትዎት በመሸሽ በዓት አጽንተው ከዓለም ተገልለው በፆም በጸሎት በቁመት በስግደት በተባሕትዎ እግዚአብሔርን ለማገልገል የወሰኑ ሰዎች የሚባትሉበት ቦታ ነው።

መነኩሴ ማለት መናኝ ብቻውን የሚኖር በንጽሕና ሆኖ ገዳማዊ ሕይወትን የሚወድ ሰው ባተሌ ከዓለም ከዘመድ ከሕዝብ ከገንዘብ የተለየ ራሴን (መላ አካሌን) ለእግዚአብሔር ስጥቻለሁ ብሎ/ ቃል ኪዳን የገባ አስኬማ መላእክት የለበሰ ባሕታዊ ማለት ነው (“መጽሐፈ ሰዋሰው ውግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ” በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ)።

## 1 ስሪት

ገዳሙ የአንድነት ገዳም በመሆኑ ጠንካራ የአንድነት ሥርዓት አለው፡፡ በዚህ ገዳም ቁሪት አጥብቆ የተከለከለ ነው፡፡ ማንኛውም የገዳሙ ማኅበር አባል የግል ሀብት (ቁሪት) ካለው ቁሪቱን ለገዳሙ ይስረክባል። ገዳሙን ለቆ ሲሄድም ሆነ በሞት ሲለይ ንብረቱን ለሌላ ለሦስተኛ ወገን በዉርስም ሆነ በሌላ በመንኛውም ሁኔታ ማስተላልፍ አያቻልም። ማንኛውም የገዳሙ አባል በገዳሙ በተዘጋጀው የስስምንት ቅጽ ላይ ወዶ ፈቅዶ ሲፈርም ያለውን ቁሪቱን ማሳወቅና ለገዳሙ ገቢ መደረግ ያለብትን ሀብቱን ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል። የግል ሀብት (ቁሪት) ተንቀሳቃሽ ሆነ የማይንቀሳቀስን ይጨምራል። ይህም ቤት ንብረትን እንዲሁም በሸርክና የሚገኝ ሀብት የጡረታ አበል ኢንሹራስ ሶሻል ሰኩሪቲ ወዘተ ይጭምራል።

### 2 ሥርዓተ ምንኩስና

ምንኩስና ማለት ከዓለም ርቀው ንጽሕ ጠበቀው የዚህን ዓለም ሀብት ንብረት ንቀው የክርስቶስን መስቀል ለመሸከም ወስነው በገዳም የሚኖሩ አበው በሕብረት (በአድነት) የሚኖሩበት ሥራዓት ነው። ምንኩስና በፈቃድ የሚቀበሉት ትእግስትን፤ ታዛዥነትን መትጋትን የሚጠይቅ ሥራዓት ነው። (ኢኦተቤክ የአድነት ገዳም መተዳደርያ ደንብ ጥቅምት 20፣ 2010)።

**በዚህ ገዳም በምንኩስና ለመኖር የሚያስፈልገው መስፈርትና መሟላት ያለባቸው ሂደቶች**

2.1 **የኦርቶዶክስ ተዋህዶ መነኩሴ**

መስፈርት

- በኦርቶዶክስ ተዋህዶ (በኢኦተቤክ ወይንም በእህት አብያተ ክርስትያናት) ሕግና ሥርዓት መሠረት በመንኩስና የቆየ
- የግል ሀብት ያለው ከሆነ ሙሉ ንብረቱን ለገዳሙ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ
- ያልተከፈለ የማንኛውም አካል (ግለሰብ ድርጅት፣ የመንግስት ተቋም ወዘተ) ዕዳ የሌለበት እንደዚሁም ምንም አይነት የሚከፈል የገንዘብ ግዴታ (የመጦርያ የህክምና ወዘተ ) የሌለበት
- በዚህ ገዳም በአበው በሕብረት (በአድነት) ለመኖር የመረጠበትን ምክንያት ለገዳሙ አርድዕቶች በቃል ለማስረዳት ፈቃደኛ የሆነ
- ማንነቱን የሚገልጽ ህጋዊና ግዜው ያላለፈበት መታውቅያ ማቅረብ የሚችል
- በአሜሪካ ሀገር ህጋዊ የመኖርያ ፈቃድ ያለው

- በገዳሙ ደንብ ለመተዳደር ፈቃደኛ የሆነ፣

ሂደት

- በገዳሙ አርድዕቶች ማንነቱን የሚያስረዱ መረጃዎችን ከመረመሩ በኋላ የመጀመርያ የቃል ምርመራ ይደረግለታል
- ሙሉ የጤንነት (የስነ አእምሮ የውጥ ደዌ የጥርስ ወዘተ) ምርመራ በገዳሙ ሓኪሞች ያደርጋል
- የገዳሙ አርድዕቶች የቀረበውን መረጃ መርምረው የመረጃውን ትክክለኝነት የሚጠቁም ሀሳብ ሲያገኙ ቢያንስ ለስድስት ወራት ነገር ግን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ግዜ በእንግድነት እንዲቆይ ይፈቀድለታል
- የቀረበው የማንነቱና የሀብቱ መረጃ ትክክለኛነት ገዳሙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ያጣራል
- ስለገዳሙ ደንብና ሥርዓት እንዲሁም ስለ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችና ሥራወች በገዳሙ አርድዕቶች ማብራርያ የሰጠዋል
- ቢያንስ ለስድስት ወራት በገዳሙ በእንግድነት ሲቆይ የገዳሙ አርድዕቶች ጠባዩን ሀይማኖቱን ቁርጠኝነቱንና ትእጋቱን የመረምራሉ፤
- በሀይማኖቱ በጠባዩና በምግባሩ መሰረታዊ ችግር ካልታየበት በገዳሙ አስተዳደር መምህር/ የገዳሙ አበምኔት ፈቃድ ሙሉ ገዳሙን እንዲጎበኝ ይፈቀድለታል። ይህም ጉብኝት የገዳሙን የአስተዳድር መዋቅር ደረጃ በደረጃ ከገዳሙ አስተዳደር መምህር ጀምሮ የምርፋቅ አባቶች፣ ጸሐፊ፣ መጋቢ፣ ሂሣብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥ፣ እቃ ቤት ጠባቂ ሊቀ አርድዕትና ሌሎችን ፣ ይጎበኛል አስፈለጊ ከሆነም አንዲያነጋግራቸው የፈቀድለታል፡፡ ውስጠ ደንቡን እንድያነብ ይደረጋል፤ የገንዘብ እና የዕቃ ወጪ አጠባበቅ፣ የገዳሙ ሥራና ስለ ገዳሙ ፀጥታ አጠባበቅና ቅጣት፣ የአዲስ አባላት አቀባበል፣ ወደ ገዳሙ ስለሚመጡ እንግዶች፣ ስለ ወንዶችና ሴቶች ገዳም ክልል፣ስለ ገዳሙ አርድዕቶች፣ ስለ ባህታውያን፣ ስለ ውርስ ገንዘብ፣ ስለ ልማት፣ ስለ ትምህርት፣ ስለ መቁነንና የአመት ልብስ፣ ስለ ስብሰባ፣ ስለ ፈቃድ፣ ስለ ጸሎተ ማኅበር፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ ስለ ግል ቁሪት፣ በስፋት ይጎበኛል በቂ ማብራርያም የሰጠዋል፡፡
- በገዳሙ አርድዕቶች አቅራቢነት የገዳሙ አስተዳደር መምህር የቃል ምርመራ ያደርጉለታል
- የገዳሙ አስተዳደር መምህር ከገዳሙ የአስተዳር ኃላፊዎች በተለይም ከመጋቢው ከገበዙ ከዋና ጸሐፊ ከሒሳብ ሹምና ከሊቀ አርድዕት እንዲሁም እንግዳ መነኪሴውን ሲከታተሉት ከነበሩት የገዳሙ አርድዕቶች መረጃዎችን ካጠነከረ በኃላ እንግዳው በጽሁፍ በዚህ ገዳም በአበው በሕብረት (በአድነት) ለመኖር የመረጠበትን ምክንያት በመመዘርዘር ማመልከቻ እንዲያስገባ ይፈቅዱለታል
- በገዳሙ አስተዳደር መምህር አማካኝነት ማምልከቻውን ለገዳሙ የአስተዳደር ጉባይ ያቀርባል
- ማመልከቻው የአስተዳደር ጉባየውን ፈቃድ ካገኘ በገዳሙ ሥርዓት አበው መሠረት የገዳሙን የአድነት ጸሎተ ማርያምን ዝቅ ብሎ ተቀብሎ ወደ ገዳሙ አንድነት ይገባል።
- ሙሉ የማኀበረ መነኮሳቱ አባል የሚሆነው ቢያንስ ሁለት ዓመት በገዳሙ ከቆየና በቆይታው ምንም አይነት ለሙሉ አባልነት የሚከለክለው የምግባር ችግር የሀይማኖቱ ህጸጽ የጠባይ ጉድለት የአይምሮ መታወክ ከሌለበትና የገዳሙን መተዳደርያ ደንብ ሙሉ በሙሉ አክብሮ ሲገኝ ብቻ ነው። በዚህ የሁለት ዓመት ቆይታው በማኀበረ መነኮሳት ጉባየ የመምረጥም ሆነ የመምረጥ መብት አይኖረውም።

**2.2 የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ**

*መስፈርት*

- በኦርቶዶክስ ተዋህዶ (በኢኦተቤክ ወይንም በእህት አብያተ ክርስትያናት) አማኝ የሆነ

- በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነቱ ሃይማኖታዊ ህፀጽ የሌለበት፣
- በሙሉ የአይምሮ ጤንነት የሚገኝ
- ዕድሜው ከ25 እስከ 70 የሆነ
- ትክክለኛ ዕድሚውን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ ይኖርበታል
- ዕድሜአቸው ከ25 ዓመት በታች የሆኑና እራሳቸውን ያልቻሉ ልጆች የሌሉት
- በትዳር ውስጥ የሌለ
- ከሀብቱ ቢያንስ አንድ ሦስተኛውን ለገዳሙ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ የቀረውን ሀብቱን ግን ለወደደው (ለገዳሙ ጭምር) መስጠት ይችላል
- ላለው ሀብት እንዲሁም ለሌሎች ላወረሰው ንብረት ማረጋገጫ ያቀርባል
- ለገዳሙ ለሰጠው ሀብት የንብረት ዝውውር ያደርጋል
- ያልተከፈለ የማንኛውም አካል (ግለሰብ ድርጅት፣ የመንግስት ተቋም ወዘተ) ዕዳ የሌለበት እንደዚሁም ምንም አይነት የሚከፈል የገንዘብ ግዴታ (የልጅ ማሳደግያ የመጦርያ የህክምና ወዘተ ) የሌለበት
- በወንጀልም ይሁን በፍታብሔር በፍርድ ቤት ይሁን በማንኛውም የጸጥታ አካል የማይፈለግ። ምንም አየነት ያልተዘጋ የፍርድ ቤት ይሁን የጸጥታ አካላት ጉዳይ የሌለበት
- በገዳሙ ደንብ ለመተዳደር ፈቃደኛ የሆነ፣
- ማንነቱን የሚገልጽ ህጋዊና ግዜው ያላለፈበት መታውቅያ ማቅረብ የሚችል
- በአሜሪካ ሀገር ህጋዊ የመኖርያ ፈቃድ ያለው

ሂደት

“ማንም ሰው ቢሆን ምንም መንፈስዊ ኃይልና የጋለ ሐሳብ ቢኖረውም ፈጥኖ ምንኩስና መቀበልም ሆነ መስጠት ክልክል ነው” (ፍትህ መነፈሳዊ አንቀ 10)

- በገዳሙ አርድዕቶች ማንነቱን የሚያስረዱ መረጃዎችን ከመረመሩ በኋላ የመጀመርያ የቃል ምርመራ ያደርጉለታል
- ሙሉ የጤንነት (የስነ አእምሮ የውጥ ደዌ ሃጥርስ ወዘተ) ምርመራ በገዳሙ ሓኪሞች ያደርጋል
- የገዳሙ አርድዕቶች የቀረበውን መረጃ መርምረው በቃል ምርመራው የመረጃውን ትክክለኝነትና ለምንኩስና የሚከለክለው መሰረታዊ ጉዳይ አለመኖሩን የሚጠቁም ሀሳብ ሲያገኙ ቢያንስ ለአምስት ወራት በእንግድነት እንዲቆይ ይፈቀድለታል
- የቀረበው የማንነቱ የቤተሰቡና የሀብቱ መረጃ ትክክለኛነት ገዳሙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ያጣራል
- ከምንኩስና የሚከለክለው የቤተሰብ ጉዳይ አለመኖሩን በመረጃ ገዳሙ ያረጋግጣል
- ስለገዳሙ ደንብና ሥራዓት እንዲሁም ሰለ ልዩ ልዩ አገልጉሎቶችና ሥራወች በገዳሙ አርድዕቶች ማብራርያ የሰጠዋል
- ቢያንስ ለአምስት ወራት በገዳሙ በእንግድነት ሲቆይ የገዳሙ አርድዕቶች ጠባዩን ሀይማኖቱን ቁርጠኝነቱንና ትእጋቱን የመረምራሉ፤
- በጠባዩና በምግባሩ መሰረታዊ ችግር ካልታየበት በገዳሙ አስተዳደር መምህር/ የገዳሙ አበምኔት/እመምኔት ፈቃድ ሙሉ ገዳሙን እንዲጎበኝ ይፈቀድለታል። ይህም ጉብኝት የገዳሙን የአስተዳድር መዋቅር ደረጃ በደረጃ ከገዳሙ አስተዳደር መምህር ጀምሮ የምርፋቅ አባቶች፣ ጸሐፊ፣ መጋቢ፣ ሂሣብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥ፣ እቃ ቤት ጠባቂ ሊቀ አርድዕትና ሌሎችን ፣ ይጎበኛል አስፈለጊ ከሆነም አንዲያነጋግራቸው የፈቀድለታል፡፡ ውስጠ ደንቡን እንድያነብ ይደረጋል፤ የገንዘብ እና የዕቃ ወጪ አጠባበቅ፣ የገዳሙ ሥራና ስለ ገዳሙ ፀጥታ አጠባበቅና ቅጣት፣ የአዲስ አባላት አቀባበል፣ ወደ ገዳሙ ስለሚመጡ እንግዶች፣ ስለ ወንዶችና ሴቶች ገዳም ክልል፣ስለ ገዳሙ አርድዕቶች፣ ስለ ባህታውያን፣ ስለ ውርስ ገንዘብ፣ ስለ ልማት፣ ስለ ትምህርት፣ ስለ መቁነንና የአመት ልብስ፣ ስለ ስብሰባ፣ ስለ ፈቃድ፣ ስለ ጸሎተ ማኅበር፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ ስለ ግል ቁሪት፣ በስፋት ይጎበኛል በቂ ማብራርያም የሰጠዋል፡፡
- በገዳሙ አርድዕቶች አቅራቢነት የገዳሙ አስተዳደር መምህር የቃል ምርመራ ያደርጉለታል። ይህም አበው አንድ ሰው ምንኩሶ በገዳሙ ለመኖር በመጣ ግዜ አበምኔቱ ጽኑ የሆነ ጥያቄ ይጠይቀው በአሉት መሰረት ነው (ፍ.ነ.አንቀጽ 10)

- የገዳሙ አስተዳደር መምህር ከገዳሙ የአስተዳር ኃላፊዎች በተለይም ከመጋቢው ከገበዙ ከዋና ጸሐፊ ከሒሳብ ሹምና ከሊቀ አርድዕቱ እንዲሁም እንግዳውን ሲከታተሉት ከነበሩት የገዳሙ አርድዕቶች መረጃዎችን ካጠነከረ በኃላ እንግዳው በጽሁፍ በዚህ ገዳም በአበው በሕብረት (በአድነት) ለመኖር የመረጠበትን ምክንያት በመዘርዘር ማመልከቻ እንዲያስገባ ይፈቅዱለታል
- በገዳሙ አስተዳደር መምህር አማካኝነት ማምልከቻው ለገዳሙ የአስተዳደር ጉባይ ይቀርባል
- የአስተዳደር ጉባየውን ፈቃድ ካገኘ በገዳሙ ሥርዓተ አበው መሠረት የገዳሙን የአድነት ጸሎተ ማርያምን ዝቅ ብሎ ተቀብሎ ወደ ገዳሙ አንድነት የገባል።
- ምንኩስና ከመቀበሉ አስቀድሞ በፈቃደ ሥጋና በፈቃደ ነፍስ መካከል ያለው ፆር ውጤቱ በምን ክፍል እንደደረሰ አስኪታዎቅ ድረስ ፈቃደ ሥጋ በርድዕና በልዩ ልዩ የትሩፋት ሥራዎች ማድከምና በትምህርት መጠንከር ስለሚያስፈልግ ከመመንኮሱ በፊት በአመክሮ ይቆያል
- በአመንክሮ ቆይታው ፈቃደ ነፍስን በሰጊድና ቅዱሳት መጽሕፍትን በመመልከት አይምሮውን ያጎለምሳል። ፈቃደ ሥጋውን ደግሞ በርድዕና በልዩ ልዩ የትሩፋት ሥራዎች ያደክማል።
- ከትዳር ዓለም ቆይቶ የመጣ ወይንም ፈለገ ሕይወት ያልቆየ ከሆነ አምስት ዓመት በገዳሙ በተለያዩ አገልግሎቶች እየተመደበ በተግባር ይፈተናል።
- የመጣው ከፈለገ ሕይወት (ከመንፍሳዊ ትምህርት ቤት ወይንም በክህነት የነበረ ወይንም በቤተ ክርስትያን አገግሎት የቆየ) ከሆነ የአመክሮ ጊዜው ሦስት ዓመት ሊሆን ይችላል
- በአመንክሮ ለሚገኝ ለማንኛውም መናኝ መካሪ ደጋፊና አስተማሪ የሆነ አባት ይመደብለታል።
- በዚህ ገዳም የመጀመርያ ደረጃ አመንክሮ **መንኖ ጥሪት** ሁለተኛው **ደቂቀ ዮሐንስ** ሦስተኛ ደረጃ ደግሞ **ቤተ ተክለሃይማኖት**;.ይባላል
- የሦስቱ የአመንክሮ ደረጃዎች የቆይታ ግዜ እንደሚከተለው ይሆናል፤ መንኖ ጥሪት ለሁለት ዓመት ደቂቀ ዮሐንስ ለሁለት ዓመት ቤተ ተክለሃይማኖት ደግሞ ለአንድ ዓመት ይሆናል
- ከፈለገ ሕይወት ለመጣ መናኝ ግን ሦስቱም የአመንክሮ ደረጃዎች እያንዳንዳቸው አንድ ዓመት ይሆናሉ።

- *ሀ.* ***መንኖ ጥሪት***;
    - ከሀብት ከንብረት ተለይተው የፈቃድ ነድያን የሆኑ ብፁዓን ናቸው (ማቴ 5፤3) የተባለላቸው ናቸው
    - ዓለሙን ከነጣዕሙ ንቀው መጥተዋልና አሁን ደግሞ እራሳቸውን ለክርስቶስ ሃይማኖት መሥዋእት አድርገው እንዲኖሩ በመንኖ ጥሪት ሥራዐት የሚገኙ ወጣንያን ብዙ እንዲማሩ መጽሐፍ አብዝተው እንዲመራመሩ ይደረጋል
    - ከሀብት ከንብረት ተለይተውና ዓለምን ንቀው ገና ምምጣታቸው ስለሆነ ወጣንያን ይባላሉ
    - መጽሕፍተ መነኮሳትን በማንበብ በጸሎት እንዲተጉ ይገባል በተለይ ብዙውን ግዜ በወጣኝነት ወቅት ፊልክስዩስን (ገብረ ክርስቶስ) በደንብ አንዲያነቡና አንዲያውቁ መደረግ አለበት ምጽሐፉ የአበውን ዜናቸውንና ታሪካቸውን በስፋት ይናገራልና።
    - አብዝተው ከአበው ምክር አንዲያገኙ ከህየወታቸው አንዲማሩ ሁኔታዎች መመቻቸት አለበት
    - የገዳሙን ሥርዐተ ጸሎት ቢያንስ መሰረታዊ የሆኑቱን ያጠናሉ
    - ለህክምና ካልሆነ በቀር ለገዳሙ አገልግሎትም ቢሆን ከገዳሙ ቅጽር ግቢ አንዲወጡ አይፈቀድላቸውም
    - ከተመደበላቸው አበው ጋር በየቀኑ እየተገናኙ ስለውሎአቸው ምክር መስማት ቡራኬ መቀበል አለባቸው
    - አበምኔቱ ቢያንስ በሳምንት አንድ ግዜ በመንኖ ጥሪት ሥርዐት የሚገኙ ወጣንያን አግኝቶ ማነጋገር ጥያቄዎቻቸውን መመለስና ቡራኬ መስጠት አለበት
    - በመንኖ ጥሪት ሥርዐት የሚገኙ ወጣንያን የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ከፈጽሙ በኃላ ሌላ ሥራ በመጨመር በትሩፋት መሥራት ይችላሉ። ነገር ግን ከሥራ ይልቅ የበለጠ ለትምህርት ለምክር ለጸሎትና መጽሐፍትን ለመርመር ግዜአቸውን አንዲጠቀሙ መደረግ አለበት
    - የአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ አመክሮውን የገመግማሉ። ገምግመው ሲያጠናቅቁ አበው ማኅበረ መነኮሳት በተገኙበት ጸሎት ይደርሳል ከዚያም ወጣንያኑ ከመንኖ ጥሪት ሥርዐት ወደ ደቂቀ ዮሐንስ ይሸጋገራሉ።
    - በገዳሙ ውስጥ የመንኖ ጥሪት ሥርዐትን በጥሩ ገዳማዊ ህይወት ላላጠናቀቁ ተጨማሪ የአመንክሮ ግዜ ሊሰጣናቸው ይችላል

- በዚህ ዓለም በሥጋ ከማገኘው ክብርና ብዕል ሁሉ ክርስቶስን በመከተል በሰማያዊ ዓለም የማገኘው ጸጋና የመንግስተ ሰማያት ክብር የበልጥብኛል ብሎ ሀብት ንብረቱን ሁሉ ትቶ ከመጣ በኋላ በመንኖ ጥሪት ሥርዐት ባገኘው ትምህርትና የህይወት ፈተና የምንኩስና ኃላፊነትን ልዘልቀው አልችልም አሰናብቱኛ ካለ ጸሎት ተደርጎለት ከአበው በረከት ተቀብሎ በፍቅር ይሸኛል።

❖ ለ. **ደቂቀ ዮሐንስ** (መጥምቅ);

- ከዓለማዊ ተግባር እርቆ ንጽሕናን ጠብቆ በመኖር የመላእክትን ኑሮ እኖራለሁ ሰውነቴን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሰጥቻለሁ ብሎ ለመኖር ወደ ምክኩስና ሕይወት እየሄደ ስለሆነ ደቂቀ ዮሐንስ ደረጃ የደረሱ ግዜአቸውን በተባሕትዎ (በብቸኝነት) እንዲያሳልፉ ይደረጋል
- ደቂቀ ዮሐንስ ደረጃ ከደረሱ በኃላ መናኝ ተበለው መጠራት ይችላሉ
- ደቂቀ ዮሐንስ ደረጃ የደረሰ መናኝ የዓለምን ነገር እየረሳ ይመጣል። ስለሆነም አርምሞ እንዲያደርግ ይደረጋል።ቢችል ደግሞ ጽማዌ ይለማመዳል። አርምሞ የአፍ ዝምታ ነው ጽማዌ ግን የልብ ዝምታ ነው።
- አርምሞን በማድረግ ጽማዌን በመለማመድ የኲነኔ ደረጃውን እያየ እንዲመጣ ይደረጋል። ኲነኔ ማለት ገዛ ማለት ሲሆን ክርስትያን ሥጋውን ለነፍሱ ማስገዛቱን ለማሳየት ነው።
- በአርምሞ በተባሕትዎ ረጅም ግዜ ሲያሳልፉ እራሳቸውን ለክርስቶስ ሃይማኖት መሥዋእት አድርገው እንዲኖሩ ጽማዌ እንዲኖራቸው ደቂቀ ዮሐንስ የሚገኙ መናንያን መጽሀፍ አብዝተው እንዲመራመሩ ይደረጋል
- መጽሕፍተ መነኮሳትን በማንበብ በጸሎት አንዲተጉ ይገባል በተለይ በዚህ የምነና ደረጃ ማር ይስሐቅን በደንብ አንዲያነቡና አንድያውቁ መደረግ አለበት ምጽሐፉ የአበውን ጾራችውንና ግብራቸውን አብዝቶ ይናገራልና።
- የገዳሙን ሥርዐተ ጸሎት ቢያንስ መሰረታዊ የሆኑቱን በደንብ ማወቅ ይኖርባቸዋል
- ለህክምና ካልሆነ በቀር ለገዳሙ አገልግሎትም ቢሆን ከገዳሙ ቅጽር ግቢ አንዲወጡ አይፈቀድላቸውም
- ከተመደበላቸው አበው ጋር በሦስት ቀን አንድ ግዜ እየተገናኙ ስለውሎአቸው ምክር መስማት ቡራኬ መቀበል አለባቸው
- አበምኔቱ ቢያንስ በወር አንድ ግዜ ደቂቀ ዮሐንስ ደረጃ የደረሱ መናኞችን አግኝቶ ማነጋገር ጥያቄዎቻቸውን መመለስና ቡራኬ መስጠት አለበት
- በደቂቀ ዮሐንስ የሚገኙ መናንያን የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ከፈጽሙ በኃላ ሌላ ሥራ በመጨመር በትሩፋት መሥራት ይችላሉ። ነገር ግን ከሥራ ይልቅ የበለጠ ለተባሕትዎ ለጸሎትና መጽሐፍትን ለመርመር ግዜአቸውን አንዲጠቀሙ መደረግ አለበት
- የአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ አመክሮውን የገመግማሉ። ገምግመው ሲያጠናቅቁ አበው ማኅበረ መነኮሳት በተገኙበት ጸሎት ይደርሳል ከዚያም መናንያን ከደቂቀ ዮሐንስ ወደ ቤተ ተክለሃይማኖት ይሸጋግራሉ።
- በገዳሙ ውስጥ የደቂቀ ዮሐንስ የአርምሞ ደረጃ በጥሩ ገዳማዊ ህይወት ላላጠናቀቁ ተጨማሪ የአመንክሮ ግዜ ሊሰጣናቸው ይችላል
- በዚህ ዓለም በሥጋ ከሚገኘው ክብርና ብዕል ሁሉ ክርስቶስን በመከተል በሰማያዊ ዓለም የማገኘው ጸጋና የመንግስተ ሰማያት ክብር የበልጥብኛል ብሎ ሀብት ንብረቱን ሁሉ ትቶ ከመጣ በኋላ በደቂቀ ዮሐንስ ባገኘው ትምህርትና የህይወት ፈተና የምንኩስና ኃላፊነትን ልዘልቀው አልችልም አሰናብቱኛ ካለ ጸሎት ተደርጎለት ከአበው በረከት ተቀብሎ በፍቅር ይሸኛል።

❖ ሐ. **ቤተ ተክለሃይማኖት**;

- ቤተ ተክለሃይማኖት የአማንክሮ ደረጃ የደረሱ መናንያን ብዙ ግዜአቸውን በትሩፋት አንዲያሳልፉ ይደረጋል። በዚህ የትሩፋት ሥራቸው ግን የበለጠ ትኩረት የሚሰጠው ተአዝዞ ማድረግና አርምሞ ማጽናትን እንዲለማመዱ ይሆናል
- በተአዝዞ ሲመሰከርላቸው አርምሞን ሲያጽኑ ጽማዌን ሲያጠነክሩ የኲነኔ ደረጃቸው ከፍ ይላል ማለትም ሥጋቸውን ለነፍሳቸው ማስገዛትን እያጸኑ ይመጣሉ።
- በቤተ ተክለሃይማኖት የሚገኙ መናንያን የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ከፈጽሙ በኃላ ትሩፋት እንዲፈጽሙ መደረግ አለበት

- መጽሐፍ አብዝተው እንዲመራመሩ ይደረጋል። መጽሕፍተ መነኮሳትን በማንበብ በጸሎት እንዲተጉ ይገባል። በተለይ በዚህ ያመንክሮ ደረጃ የገዳማዊ ህይወት ጣዕምን መቅመስ ጀምረዋልና አረጋዊ መንፈሳዊን በደንብ እንዲያነቡና እንድያውቁ መደረግ አለበት። አረጋዊ መንፈሳዊን የአበውን ጸጋቸውናን መዓረጋቸውን አብዝቶ ይናገራል።
- አብዝተው ከአበው ምክር እንዲያገኙ ከህየወታቸው እንዲማሩ ሁኔታዎች መመቻቸት አለበት
- የቤተ ተክለሃይማኖት መናንያን የገዳሙን ሥርዐተ ጸሎት አጠናቀው ሊያውቁ ይገባል።
- ለህክምና ካልሆነ በቀር ከገዳሙ ቅጽር ግቢ እንዲወጡ አይፈቀድላቸውም ነገር ግን ለመፍቅደ ደብር በአበ ምኔቱ ፈቃድ ከአንድ ቀን ላልበለጠ ግዜ ምውጣት ይችላሉ
- ከተመደበላቸው አበው ጋር በየዕለቱ እየተገናኙ ስለውሎአቸው ምክር መስማት ቡራኬ መቀበል አለባቸው
- አበምኔቱ ቢያንስ በሳምንት አንድ ግዜ የቤተ ተክለሃይማኖት መናንያን አግኝቶ ማነጋገር ጥያቄዎቻቸውን መመለስና ቡራኬ መስጠት አለበት

**ማጠቃልያ፡ ሦስቱ የአመንክሮ ደረጃዎች**

| ምን ይጠበቃል \ ደረጃ | **መንኖ ጥሪት** | **ደቂቀ ዮሐንስ** | **ቤተ ተክለሃይማኖት** |
|---|---|---|---|
| የቆይታ ግዜ | ሁለት ዓመታት | ሁለት ዓመታት | አንድ ዓመት |
| የቆይታ ግዜ (ከፈለገ ህይወት ለመጣ) | አንድ ዓመት | አንድ ዓመት | አንድ ዓመት |
| ስያሜ | ወጣኒ | መናኝ | መናኝ |
| የገዳሙ ሥርዐተ ጸሎት ዕውቀት | ቢያንስ መሰረታዊ የሆኑቱን ያጠናሉ | መሰረታዊ የሆኑቱን ያጠናቅቃሉ | የገዳሙ ሥርዐተ ጸሎት ያውቃሉ |
| ትኩረት | ትምህርት፤ ምክር፤ ጸሎትና መጽሐፍትን መመርመር | ተባሕትዎ፤ አርምሞ ጽማዌ | ትሩፋት፤ተአዝዞ፤ |
| መጽሕፍተ መነኮሳት | ፊልክስዮስን በደንብ ማንበብና ማወቅ | ማር ይስሐቅን በደንብ ማንበብና ማወቅ | አረጋዊ መንፈሳዊን በደንብ ማንበብና ማወቅ |
| የተመደበው አበው ጉብኝት | ዕለት ዕለት | በሦስት ቀን አንድ ግዜ | ዕለት ዕለት |
| የአበምኔቱ ጉብኝት | ቢያንስ በሳምንት አንድ ግዜ | ቢያንስ በወር አንድ ግዜ | በሳምንት አንድ ግዜ |
| አጽንዖ በዓት | ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት አይፈቀድም | ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት አይፈቀድም | ለመፍቅደ ደብር ከአንድ ቀን ላልበለጠ ግዜ |

**ምንኩስና**

- ❖ የቤተ ተክለሃይማኖት መናንያን አመክሮውን ሲፈጽም ለምንኩስና ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ
- ❖ አበው ማኅበረ መነኮሳት አመክሮውን ገምግመው ለምንኩስና የተገባ መነፈሳዊነት ያለው ሰው ሆኖ የተገኘ እንደ ሆነ ማኅበሩ ሁሉም የገባዋል ብለው ሲመሰክሩለት ሥራዓተ ምንኩስና እንዲፈጸምለት ይወሰናል።
- ❖ አበው ገዳማውያኑም የምንኩስና ሕይዎት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ በዝርዝር ደጋግመው ያስረዱታል።
- ❖ እርሱም በመጀመርያ በቃል በኃላ በጽሁፍ እናንተን ያስቻለ እግዚአብሔር እኔንም ያስችለኝ በእናንተ ጸሎት በእመ ብርሃን እርዳታ በእግዚአብሔር ኃይልም እችለዋለሁ ካለ የገዳሙን ስምረት አድረን የምንኩስና ሥራዓት ይፈጸምለታል።
- ❖ ይህም የሚደረገው አበው ሠለስቱ ምእት "ምንኩስና የፈቃድ እንጂ በግዴታ የምትሆን አይደለችም " ስላሉ መናኙ በፍጹም የግል ፈቃዱ ያለምን የሌላ ሰው ጫና እንዳይመነኩስ ለማረጋገጥ ነው።
- ❖ ተጨማሪ የአመክሮ ግዜ ካስፈለገው ግን አበምኔቱ ወስነው ይፈቅዱለትና በቤተ ተክለሃይማኖት ይቆያል።
- ❖ ነገር ግን የተዘረዘርውን የምንኩስና ኃላፊነት ሰምቶ ልዘልቀው አልችልም ካለ ከማኅበረ መነኮሳቱ ይሰናበታል ከማኅበረ መነኮሳቱ ከተሰናበተ ለገዳሙ ያወረሰው ሀብት ተመላሽ አይሆንም። ከገዳሙ የሚሰናበት ከሆነ በአበምኔቱ ፊርማ በተጻፈ መሸኛ ደብዳቤ ይሰናበታል።

- የአመክሮ ግዜውን አቋርጦ ከገዳሙ የለቀቀ ወይንም በተለያየ ምክንያት የተሰናበተ ሰው ተመልሶ ወደ ገዳሙ ቢመጣና ምን አልባት ተፈቅዶለት ወደ ገዳሙ ቢመለስ እንደ አዲስ አመልካች በእያንዳንዱ ሂደት ማለፍ ይኖርበታል።
- በገዳሙ ውስጥ የአመክሮ ጊዜያቸውን በጥሩ ገዳማዊ ህይወት ላሳለፉ አባቶችና እናቶች በጰራቅሊጦስ እና በቅድስት አርሴማ ዓመታዊ በዓል (መስከረም 29) ሥርዓተ ምንኩስና ይፈጸማል።
- በቤተ ክርስትያን ሥርዓት መሰረት የምንኩስና መዓረግ ይሆኑትን ቆብና ቅናተ ዮሐንስ የመስጠት ስልጣን የገዳሙ አበ ምኔት ነው

## 3 ጸሎተ ማኅበር

- በገዳሙ የጸሎት ሥርዓት በቀን ሰባት ጊዜ የሚደርስ ሲሆን፤ እነዚህም ጠዋት በ3፣ በ6፣ በ9፣ በ11፣ እና ማታ በ3፣ በ6፣ በ9 ናቸው፡፡
- በገዳሙ የዕለት ሥራ ምክንያት በገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት የማኅበር ጸሎት መገኘት ያልቻሉ መነኮሳት ከሌሊቱ አሥራ አንድ ሰዓትና በሠርክ (11 ሰዓት) ከቤተ ክርስትያን በሚደረገው ጸሎት መገኘት ይኖርባቸዋል። እንደዚሁም የማታ 3፣ ሰዓትና የሌሊት 6 እና 9 ሰዓት ጸሎት ያደርሳሉ።
- እነኝህ ሁሉንም የማህበር ጸሎት በሥራ ምክንያት መሳተፍ ያልቻሉ መነኮሳት በሚገኙበት የገዳሙ የሥራ ቦታ ሁነው የቀሩትን ሰዓታት ማለትም ጠዋት 3፣ 6 እና 9 ሰዓት በለሁሳስና በግላቸው ወይም ቢጋራ በሚመቻቸው ሁኔታ ያደርሳሉ።
- በተለያየ ምክንያት ገዳማውያኑ ስብሰባ ላይ ቢሆኑ እንኳን የተመደበው የጸሎት ግዜ ቢደርስ የማኅበሩን አጭር የሥራ ቦታና የጉዞ ጸሎት ያደርሳሉ
- ማንኛውም የገዳሙ ሥራ የገዳሙን የጸሎት ሥርዓት ባከበረ መልኩ መሆን የገባዋል።
- ማንኛውም የገዳሙ የማኅበረ መነኮሳት አባል ከገዳሙ ቅጽር ግቢ ውጭ ከሆነ በየትኛውም በሚገኝበት ቦታ (በጉዞ እንኳ ቢሆን) በቀን ሰባት ጸሎት ማድረስ ይኖርበታል
- ሥርዓተ ቅዳሴው ጧት የሚከናወንባቸው ዕለታት እሁድ ቅዳሜ እና በዓለ ሃምሳ ናቸው።
- የጋራ ጸሎት ሰዓት ሲደርስ በቤተ ክርስትያን በደዎል የነገራል
- በገዳሙ አካባቢ በሚፈጠር የአየር ሁኔታና በተለያዩ ምክንያቶች በቤተ ክርስትያን በሚደረገው የጋራ የማኅበር ጸሎት የግዜ ወይንም የአካሄድ ለውጥ ማድረግ ቢያስፈልግ በሊቀ አበው አማካኝነት ይደረጋል።
- የማኅበሩ የጋራ ጸሎት እና አጭር ጸሎት (የሥራና የጉዞ ጸሎት) ሥርዓት ይበጃል።

## 4 አመጋገብ ሥርዓት

- እሁድ ቅዳሜ እና በዓለ ሃምሳ ሥራዓተ ቅዳሴው ጧት ስለሚከናወን የመቁነን ጊዜ ከቀኑ ሦስት ሰዓት እና አስር ሰዓት ይሆናል፤
- ከሰኞ እስከ ዓርብ የመቁነን ጊዜ ከቀኑ ሥድስት ሰዓት እና አሥራ ሁለት ሰዓት ይሆናል
- ፆም በሆነ ውቅት የመቁነን ጊዜ ከቀኑ አሥር ሰዓት ይሆናል
- በሰሙነ ሕማማት ምሽቱ ሦስት ሰዓት ይሆናል
- በጤንነት ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ተጨማሪ ወይም የተለየ የመቁንን ሰዓት ለሚያስፈልገው መናኝ በመጋቢው ፈቃድ አሰፈላጊው ሁሉ ሊደረግለት ይችላል።
- ወደ ምርፋቅ የሚኬድበት ሰዓት ሲደርስ የምርፋቅ ደወል ይደወላል
- መቁነን የሚደረገው ቢጋራ ነው። ምግብ በበዓት መመገብም ሆነ ማስቀመጥ አይፈቀድም በጤንነት ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት መጋቢው ፈቃድ ካልሰጠ በቀር።

❖ በታላላቅ በዓላት ማለትም ልደት ጥምቀት ትንሣኤ በመሳሰሉት ቀናት አበምኔቱ የቅዳሴ ጸሎት እንደተፈጸመ ማኀበሩን አስከትሎ ወደ ምርፋቁ ገብቶ በተዘጋጀለት ቦታ ላይ ይቆማል ። ማኀበሩም እንደዚሁ ሰደቃውን ከበው ይቆማሉ

❖ ቀጥሎ ጸሎተ ማዕድ ይጸለያል ከጸሎቱ በኋላ በየወንበራቸው ተቀምጠው የመገባሉ

❖ ተመግበው ሲጨርሱ ቅዱሳት መጻሕፍት ስንክሳር ዜና አበው እየተነበቡ እንዲሰሙ ይደረጋል።

❖ ማንኛውም አይነት የአልኮል መጠጥን በገዳሙ ክልል መጠጣት ማስገባት እና ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው።

## 5 አለባበስ ሥርዓት

❖ ስንክሳር ጥር 22 የምንኩስናን አለባበስ እንዴት እንደተጀመረ ሲገልጽ ደገኛው ቅዱስ አባ እንጦስ አስቄጥስ ገዳም ገብተው በፍጽምነት ሥራ በተባሕትዎ ሲኖሩ የሰይጣን ፈተና በተቃወማቸው ግዜ የታዘዘ መላአክ መጥቶ ወጥተህ ተመልከት አላቸው ሲመለከቱም መልአኩ አልባሰ ምንኩስናን ለብሶ ቅናተ ዮሐናስና በመስቀለኛ የተታታ አስኬማ አድርጎ በራሱም ላይ እንደ ራስ ወርቅ አምሳል ቆብ ደፍቶ አየው። አባ እንጦስም ይህንን ልብሰ ምንኩስናን እርሳቸው ለበሱ ለረዳቸው ለአባ መቃርስም አልባሰ ምንኩስናን አለበሱት

❖ መናንያኑ የሚለብሱት ልብስ ሁሉም አንድ አይነት የሆነ አሰፋፉም የገዳማውያንን ሥርዓት የተከተለ ነው፡፡

❖ የሚያደርጉት ቅናተ ዮሐንስ እና የሚደፉት አስኬማ/ቆብ አንድ አይነትና ወጥነትን የተከተለ ነው

❖ በተለያዩ በዓላት እንዲሁም ለሥራ እና ለጸሎት በገዳምውያን የሚለበሱት አልባሳት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

❖ በሦስቱም አመንክሮ ደረጃዎች ማለትም መንኖ ጥሪት ደቂቀ ዮሐንስና ቤተ ተክለሃይማኖት የሚገኙ መናያን አለባበሳቸው ከመነኮሳቱ የተለየ ይሆናል።

❖ በአመንክሮ ሦስቱ ደረጃዎች ማለትም (ሀ) መንኖ ጥሪት (ለ) ደቂቀ ዮሐንስ እና (ሐ) ቤተ ተክለሃይማኖት የሚገኙ መናንያንም አንድ አይነት አለባበስ አይኖራቸውም። አለባበሳቸው የሚገኙበትን የአመንክሮ ደረጃ የሚናገር ይሆናል።

❖ የልብሱ ቀለም አይነት እና ዲዛይን በማኅበረ ገዳሙ የሚወሰን ይሆናል። ነገር ግን የቤተ ክርስትያንን መሰረታዊ የአለባበሱን ምሳሌነት መልቀቅ የለበትም

❖ መመንኮስ ከዚህ ዓለም መሞት ነውና ቆቡ የሰበን ቀሚሱ የመጎናጸፍያ ቅናት የመግነዝ አስኬማ የትንሳኤ ሙታን ምስሌ ነው። በተጨሪም፤

- ቆብ ፤ ጌታችን በቀራንዮ የደፋው የሾህ አክሊል
- ቅናት ይህ ስቅ ገመድ ሲሆን ዮሓንስ መጥምቅ የታጠቀውና ጌታ የታሰረበት ገመድ ምሳሌ ነው
- ቀሚስ፤ የከለሜዳ ምሳሌ ነው
- አስኬማ፤ የሰውነት ምስሌ ነው።

## 6 አስተዳደራዊ እርምት

❖ የገዳሙን መተዳደርያ ደንብና በአጠቃላይ ሥርዓተ ምንኩስና በእያንዳንዱ የማኀበረ መነኮሳት አባልና በአስተዳደራዊ ጉባየ አመራር በትትክል መጠበቁን የሚከታተለው የምክረ አበው ጉባየ የሚከሰቱ አለመግባባቶች በፍቅር እንዲፈቱ፣ ጥፋቶች እንዲታረሙ የጎደሉ አሰራሮች እንዲስተካከሉ ያደርጋል

❖ በኢጋጣሚ በመናንያን መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በራሳቸው እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ በራሳቸው መፍታት ያልቻሉትን ግን ለምክረ አበው ጉባየ ይቀርባል

❖ ማንኛውም የማኀበረ መነኮሳቱ አባልም ሆነ እንግዳ መነኩሴ ወይንም በአመክሮ ላይ የሆነ መናኝ ያለምንም ሥራ (የተግባረ ዕድ ጸሎት መጽሐፍ መመልከት መጻፍ የጤንነት አንቅስቃሴ ወዘተ) መቀመጥና መሰብሰብ አይችልም።

- ድቀት ያገኘው መነኩሴ ስለ ሠራው ኃጢአት ንስሓ ተቀብሎ በመዓረጉ ተመልሶ በምኩስናው እንዲጸና አበው አዘዋል። እንደዚሁም ደግሞ ሕገ ምንኩስናውን ነቅፎ (ንቆም) በዓለም ሊኖር ወዶ ከምንኩስና ሥራዓት የወጣ ከሆነ ሕዝባወያኑን ምስሎ ይኑር አንጂ በመነኮሳት አርአያ ሊኖር አይገባም (ፍትሐ ነገ አንቀጽ ፲ ገጽ 86)

- የምግባር ሕጸጽ የተገኘበት መነኩሴ በቀኖና ቤተ ክርስትያን መሰረት ቀኖና ይሰጠዋል። ጥፋቱን ከሦስት ግዜ በላይ ከተደጋጋመና ቀደም ሲል የተሰጠውን እርምት ተቀብሎ ካላስተካከለ የምክረ አበው ጉባየ ለማኅበረ መነኮሳቱ ጉዳዩን አቅርቦ ከገዳሙ እንዲሰናበት ያደርጋል
- በገዳሙ ውስጥ በአሜሪካ ህግ በከባድ ወንጀል የሚያስቀጣ ጥፋት ከተገኘ የምክረ አበው ጉባየ ጉዳዩን ለህግ አማካሪ ቡድን ያቀርባል። የህግ አማካሪ ቡድኑ ጉዳዩን መርመሮ አሰፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት ዝርዝር ሁኔታውን ለአበምኔቱና ለምክረ አበው ጉባየ አስረድቶ ጥፋተኛውን ለሚመለከተው የአካባቢው ህግ አካላት ያቀርባል።

## 7 አጽንዖ በዓት

- አበው መነኮሳት ለምንኩስና ገድል ዋናው መሰረቱ አጽናዖ በዓት እና ተአዝዞ ናቸው ይላሉ። አጽናዖ በዓትም ያጸና መናኝ ሌላው ፈተና ድል ሊነሳው አይችልም። መነኩሴ ከበዓቱ ካልወጣ በቀር ከርእይና ከሰሚዕ የሚነሣ የፈቲው ፈቃድ አያገኘውም።

- ሰው ከሞተ በኋላ የሥጋዊን ሥራ መሥራት እንደማይችል ሁሉ መነኮሳትም ዓለምን ንቀው መንነው ገዳም ገብተው ምንኩስናን ከተቀበሉ በኃላ ከቅጽረ ገዳሙ ወጥተው መኖርና እንደ ዓለማውያን በግል ጉዳያቸው መውጣት መውረድ በሥራዓተ አበው ፈጽሞ የተከልከለ በመሆኑ በዚህ ገዳም ያሉ መነኮሳት በግል ጉዳይ ከገዳሙ ቅጽር ውጭ መውጣት በፍጹም አይፈቀድም።

- የአድነት ገዳም አበው መነኮሳት ከገዳሙ ክልል ውጪ አበ ንስሐ እንዳይሆኑ የተከለከለ ነው።

- መነኮሳት የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ጥሪ አስከሌላቸው ድረስ ከገዳሙ ቅጽር ግቢ ውጭ የሚገኝን ማንኛውንም ቤተ ክርስትያን ለማገልገል ወይንም የገዳሙ ላልሆነ ለሌላ አገልግሎት ከገዳሙ ቅጽር ውጭ መውጣት  አይፈቀድም።

- ለመፍቅደ ደብር (ለማኅበረ ገዳሙ አገልግሎት) ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት ቢያስፈልግ በመጋቢው አቅራቢነት አስከ ሦስት ቀን የሆነ ፈቃድ አበምኔቱ መስጠት ይችላሉ። ከአራት ቀን አስከ ሰባት ቀን  ፈቃድ ቢያስፈልግ ግን የገዳሙ የአስተዳደር ጉባየ በአበምኔቱ አቅራቢነት መፍቀድ ይኖርበታል።

- መጋቢው ለመፍቅደ ደብር አስከ አምስት ቀን ለሆነ ፈቃድ በአብምኔቱ ፈቃድ ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት ይችላሉ። ከስድስት ቀን እስከ አስራ አምስት ቀን ፈቃድ ቢያሰፈልገው ግን የገዳሙ የአስተዳደር ጉባየ በአበምኔቱ አቅራቢነት መፍቀድ ይኖርበታል። ነገር ግን መጋቢው ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት የሚኖርበት አበምኔቱን በመተካት ለሚደረግ አገግሎት ከሆነ የፈቃድ ግዜውና አሰጣቱ ለአበምኔቱ በሚፈቀደው የፈቃድ አገልግሎት አንቀጽ ሥር ይታያል።

- አበምኔቱ ለመፍቅደ ደብር አስከ አምስት ቀን ለሆነ ፈቃድ የአስተዳደር ጉባየውን  በማሳወቅ ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት ይችላል። ከስድስት ቀን አስከ ሰላሳ ቀን ፈቃድ ቢያስፈልገው ግን የገዳሙ የአስተዳደር ጉባየ ውሳኔና የሀገረ ስብከቱ ወይንም የገዳሙ የበላይ ጠባቂ ሊቀ ጳጳስ መፍቀድ ይኖርበታል።

- አንድ መነኩሴ በሕክምና ጉዳይ ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት ቢያስፈልገው ለገዳሙ ሀኪም የህክምና ትዕዛዝን በማቅረብ በአበምኔቱ በኩል ፈቃድ ማግኘት ይችላል.። ነገር ግን ህክምናው ከሰባት ቀን በላይ ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣትን የሚጠይቅ ከሆነ ይህን የሚያረጋግጥ የሕክምና  መረጃው ቀርቦ በገዳሙ የአስተዳደር ጉባየ በአበምኔቱ አቅራቢነት መፈቀድ ይኖርበታል። ለመታከም አስታማሚ ቢያስፈልገው የአስታማሚው መነኩሴ ፈቃድ ከታማሚው የፈቃድ ዝርዝር ጋር አብሮ ይታያል።

- ማንኛውም የገዳሙ መናኝ አበምኔቱን ጨምሮ ብቻውን ከገዳሙ ቅጽር ግቢ መውጣት አይፈቀድለትም።

❖ በተለያየ ምክንያት በአንቀጽ XX ከቁጥር XXX እስከ XXX በተጠቀሰው መሰረት ፈቃድ አግኝቶ ከገዳሙ ለአጭር ግዜ ቆይታ ለሚወጣ መናኝ ምንግዜም በሚሄድበት ቦታ አብሮት የሚሄድ ቢያንስ አንድ መናኝ ይመደብለታል።


❖ አንድ የማኅበር አባል የገዳም ነዋሪነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ወረቀት የሚያገኘው በገዳሙ ውስጥ አባል ሆኖ ቢያንስ ሁለት አመት የቆየ እንደሆነ ነው፡፡

# 7 አስተዳደራዊ መዋቅር

በገዳሙ መተዳደርያ ህገ ደንብ በተዘረዘረው አስተዳደራዊ መዋቅር መሰረት ገዳሙ የሚከተሉት የአስተዳደር መዋቅር ይኖረዋል

## 7.1 አስተዳደራዊ መዋቅር

**የገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅር**




1. **የማኅበረ መነኮሳት ጠቅላላ ጉባየ፡** ይህ በገዳሙ በቋሚ አባልነት ተመዝግበው የሚኖሩ ማኅበረ መነኮሳት ጉባየ ሲሆን በአመንክሮ የሚገኙ መናንያን ያለ ድምጽ የጉባየው አባል መሆን ይችላሉ። ጉባየው ገዳሙን በበላይነት ያስተዳድራል። በአበምኔቱ አማካኝነት ለሚቀርቡ አጀንዳዎች ውስኔዎችን ይሰጣል፤ አበምኔት ሊመርጥ ይችላል። ሌሎች የገዳሙ የአስተዳደር ኃላፊዎችን ሹመት ያጸድቃል።
2. **የአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ**፤ ይህ የገዳሙ የአስተዳደር ኃላፊዎች ጉባየ ሲሆን አባላቱም አበምኔት መጋቢ ሊቀ አበው ገበዝ ሊቀ አርድዕት ዋና ጸሐፊ ሒሳብ ሹም ንብረት አስተዳደር ቁጥጥር ዐቃቢ ንዋይ ሊቀ አረጋዊ እና ሌሎች የስተዳዳር

ኃላፊዎች ያሉበት ነው። ከጠቅላላ ጉባኤ ቀጥሎ የገዳሙን ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚቆጣጠርና የገዳሙን የዕለት ከዕለት አገልግሎት የሚመራ ሥራ አስፈጻሚ ነው።

3. **የምክረ አበው ጉባየ** ፤ የገዳሙን መተዳደርያ ደንብና በአጠቃላይ ሥርዓተ ምንኩስና በእያንዳንዱ የማኅበረ መነኮሳት አባላትና በአስተዳደር ጉባየ አመራር በትትክል መጠበቁን የሚከታተል ጉባየ ነው። የዚህ ጉባየ አባላት በቁጥር ሦስት አባላት ያሉት ሲሆን እነዚህም የቁጥጥር ኃላፊውንና በትሩፋታቸው በትጋታቸውና በዕውቀታቸው የተመሰከራላቸው ሁለት አባቶች ይሆናሉ። የምክረ አበው ጉባየ የሚሰየመው በማኅበረ መነኮሳት ጉባየ ይሆናል።
4. **የህግ አማካሪ ቡድን**፤ ገዳሙ የሜሪካን ህግ አክብሮና አስጠብቆ መሔድ እንዲችል ማንኛውም አስፈላጊ የሆኑ የህግ አገልግሎት የሚሰጥ አካል ሲሆን የቡድኑ አባላት ብዛት እንደየሁኔታ እየታየ በአስተዳደር ጉባየው የሚወሰን ይሆናል። የህግ አማካሪ ቡድን አባላት የሜሪካን ህግ ጠንቅቀው የሚያውቁ በሀይማኖታቸው የተመሰከረላቸው ለገዳሙ በነጻ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ የቤተ ክርስትያኒቷ ልጆች ሲሆኑ የማኅበረ መንኮሳት አባል እንዲሁም አባል ያልሆኑ ማንኛውም የቤተክርስትያን ልጆች ለዚህ አገግሎት ሊመረጡ ይችላሉ። ይህ የአገልግሎት ቡድን በየትኛውም የአሜሪካ ክፍል የሚኖሩ ፈቃደኞች ስብስብ ነው። የህግ አማካሪ ቡድን የአስተዳድር ጉባየ አባል አይደለም።

## 7.2 የአስተዳደር ኃላፊዎች ዝርዝር

1. አበምኔት
   - **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱ በቱሩፋቱ በስነ ምግባሩና በአስተዳድር ችሎታው የተመሰከረለትና በድንግልና መንኩሶ የቁምስና ማዕረግ ያለው
   - **አሾሻም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሾማል።
   - **ተጠሪነት፤** ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና ለማኅበረ ገዳሙ ጉባየ ይሆናል
   - **ኃላፊነት፤**
     - ገዳሙን በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል
     - ሰዓት ወስኖ መነኮሳቱን በሃይማኖት እንዲጸኑ ማስተማር
     - በዓበይት በዓላት ውቅት ውንጊል መስበክ ቀድሶ ማቁረብ ጽሎተ ቡራኬና ቃለ ምዕዳን መስጠት
     - የገዳሙን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል።የመራል።
     - የምንኩስና መዓረግ ይሆኑትን  ቆብና ቅናተ ዮሐንስ ይሰጣል።

2. መጋቢ
   - **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳሙ በቋሚነት የኖረ በዕውቀቱ በቱሩፋቱ በስነ ምግባሩና በአስተዳድር ችሎታው የተመሰከረለት መነኩሴ
   - **አሾሻም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
   - **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
   - **ኃላፊነት፤**
     - ለአበምኔቱ የቅርብ ረዳት ሁኖ ያገለግላል
     - አበምኔቱ በማይገኝበት ወቅት አበምኔቱ ከሚፈጽመው መንፈሳዊ አገልግሎት በስተቀር የአስተዳደሩን ሥራ ኃላፊነቱን በመውሰድ የሠራል
     - በዕቃ ግምጃ ቤትና በምግብ ቤት የሚያገለግሉትን ይመራል
     - ከበታች ያሉ ሹማምንት የሚያቀርቡትን የሚመከርባቸውን ጉዳዮች እየተቀበለ ለአበምኔቱ ያቀርባል። የተወሰነውንም ጉዳይ እንደ አሰፈላጊነቱ ያስፈጽማል
     - እንደሁኒታው ታይቶ የገዳሙን ልማት ሊመራና ሊቆጣጠር ይችላል።
     - የገዳሙን የውስጥ አሰተዳደራዊ እንቅስቃሴ ከአበምኔቱ ቀጥሎ ይቆጣጠራል።ይመራል።

3. ገበዝ

- **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳሙ በቋሚነት የኖረ በዕውቀቱ በቱሩፋቱ በስነ ምግባሩና በአስተዳድር ችሎታው የተመሰከረለት መነኩሴ
- **አሿሿም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
- **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
- **ኃላፊነት፤**
    - ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተመደቡትን አገልጋዮች ይመራል
    - በቤተ መቅደስ ውስጥ አገግሎት የሚሰጡ አገልጋዮችን ይመራል
    - በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሉትን ቋሚ ቅርስ ከታቦተ ሕጉ ጀምሮ የገዳሙን ንዋየ ቅድሳትን አልባሳትን መጽሐፍትን ልዩ ልዩ ንብረቶችንና ቅርሶችን የጠበቃል። ያስጠብቃል።

4. ዋና ጸሐፊ
- **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱ በስነ ምግባሩና በአስተዳድር ችሎታው የተመሰከረለት መነኩሴ ነገር ግን እንደ ሁኔታው በአመክሮ ያለ መናኝም ሊሆን ይችላል
- **አሿሿም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
- **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
- **ኃላፊነት፤**
    - የገዳሙ አሰተዳደር ጉባየ ቃለ ጉባየ ይይዛል
    - የገዳሙን ማኅተም ይይዛል
    - በገዳሙ ውስጥና ውጭ የተደረገውን የገዳሙ እንቅስቃሴ በመግለጫ ለጽ/ቤቱ ያቀርባል
    - ቃል ጉባየንና ሌሎች መዛግብት ተረከቦ ይይዛል

5. ሒሳብ ሹም
- **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱ በስነ ምግባሩና በትጋቱ የተመሰከረለት መነኩሴ ነገር ግን እንደ ሁኔታው በአመክሮ ያለ መናኝም ሊሆን ይችላል
- **አሿሿም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
- **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
- **ኃላፊነት፤**
    - የሒሳብ መዛግብትን በተሟላ ሁኔታ አዘጋጅቶ ገቢውን ወጪውን የመዘግባል
    - ገቢውና ወጪው በሕጋዊ የሒሳብ አያያዝ መሰረት መደረጉን ይቆጣጠራል
    - የሒሳብ ሠነዶችና ይይዛል
    - በየወሩ ለጽ/ቤት የሒሳብ ሪቦርት ያቀርባል

6. ንብረት አስተዳደር
- **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በስነ ምግባሩና የተመሰከረለት መነኩሴ
- **አሿሿም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
- **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
- **ኃላፊነት፤**
    - የገዳሙ ንብረት መዝግቦ ይይዛል
    - ገቢና ወጪ መሆን የሚገባቸውን ንብረቶች ይከታተላል
    - የመገልገያ ንብረቶች የአገልግሎት ዘመን የሽፋን ግዚ (warranty) እና ኢንሽራንስ ይከታተላል

7. ቁጥጥር
- **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱ በስነ ምግባሩና በአስተዳድር ችሎታው የተመሰከረለት መነኩሴ
- **አሿሿም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
- **ተጠሪነት፤** ለአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ ይሆናል
- **ኃላፊነት፤**

- ሒሳብ በአግባቡ መሰራቱን ያረጋግጣል
- የገዳሙ ንብረት አየያዝ የከታተላል
- የገዳሙ መመርያዎችና ውሳኔዎች በተገቢው መንገድ መፈጸማቸውን የከታተላል
- ለማኅበረ ገዳሙ አስፈላጊ በሆነ ግዜና በአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ ፈቃድ ካገኘ ሁሉ ሪቦርት ያቀርባል

8. ዐቃቢ ንዋይ (ገንዘብ ክፍል)
   - ❖ **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱና  በስነ ምግባሩ የተመሰከረለት መነኩሴ
   - ❖ **አሸሻም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
   - ❖ **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
   - ❖ **ኃላፊነት፤**
     - የገዳሙን የባንክ ሒሳብ የከታተላል
     - የገዳሙን የገቢና የወጪ ደረሰኞች ይይዛል

9. ሊቀ አርድዕት
   - ❖ **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱ በስነ ምግባሩና በአስተዳድር ችሎታው የተመሰከረለት መነኩሴ
   - ❖ **አሸሻም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
   - ❖ **ተጠሪነት፤** ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና ለማኅበረ ገዳሙ ጉባየ ይሆናል
   - ❖ **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
   - ❖ **ኃላፊነት፤**
     - ከመጋቢው በታች ከአርድዕቱ  በለይ ሆኖ ጠቅላላ የአርደዕቱን የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል
     - የገዳሙን የልማት እንቅስቃሴ ይመራል

10. ሊቀ አረጋዊ
   - ❖ **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቱ በስነ ምግባሩ በትጋቱ የተመሰከረለት መነኩሴ
   - ❖ **አሸሻም፡** በአበምኔቱ ተመርጠው ይሾማል
   - ❖ **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
   - ❖ **ኃላፊነት፤**
     - የማኅበረ መነኮሳት አባል የሆኑ አረጋውያንና በልዩ ልዩ ምክንያት አቅማቸው የደከሙትን እንደ ልጅ፣ ወንድምና አባት ሆኖ ይንከባከባል
     - በሰዓት ምግብ ያቀርባል። ገላቸውን ያጥባል። መድኃኒታቸውን በተገቢው መንገድ ያቀርባል። ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን አንክብካቤ ያደርጋል።
     - የማኅበረ መነኮሳት አባል የሆኑ አረጋውያንና በልዩ ልዩ ምክንያት አቅማቸው የደከሙት በገዳሙ በሚገኝ የገዳሙ አባል ያልሆኑ ከሚጦርበት ማዕከል አይካተቱም። የሚደርግላቸው እንክብካቤ የጀመሩትንና በሥጋ ዓለም የሙቱለትን፣ በመንፈሳዊ ዓለም ግን ሕያዋን የሆኑበትን የምንኩስና ህይወት ባላቸው አቅም አንዲፈጽሙ ለመርዳት እንጂ እንዲጦሩ አየደለም።

11. ሊቀ አበው
   - ❖ **የብቃት መመዘኛ፡** በአድነት ገዳም የኖረ በዕውቀቱ በቱሩፋቱ በስነ ምግባሩና በትጋቱ የተመሰከረለትና መነኩሴ
   - ❖ **አሸሻም፡** በማኅበረ መነኮሳቱ ተመርጦ በአበምኔቱ ይሾማል
   - ❖ **ተጠሪነት፤** ለአበምኔቱ ይሆናል
   - ❖ **ኃላፊነት፤**
     - በየሰዓቱ ጸሎት የሚያደርሱትን አበው ይሰበስባል
     - የየሰዓቱን ጸሎት ይመራል
     - የአበው የጋራ ጸሎት ሰዓት ይቆጣጠራል

## 7.2 የሥራ ኃልፊዎች አመራረጥና አሾሻም

የገዳሙ የሥራ ኃላፊዎች አመራረጥና አሾሻም በገዳሙ ህገ ደንብ መሰረት ይሆናል

## 7.3 የማኅበረ መነኮሳት ጠቅላላ ጉባየ

የገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት ጠቅላላ ጉባየ ስልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም የስብሰባ ግዜና የስብሰባ አጠራር በገዳሙ ህገ ደንብ መሰረት ይሆናል

## 7.4 የአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ

የአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ ስልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም አስራር በገዳሙ ህገ ደንብ መሰረት ይሆናል።

# 8 የማኅበረ መነኮሳት መብትና ግዴታ

**መብት**

- በማኅበረ መነኮሳት ሙሉ አባልነት ተመዝግቦ የሚገኝ መነኩሴ በገዳሙ የተለያዩ ኃላፊነቶች የመመረጥና የመምረጥ መብት አለው
- ነገር ግን የምከረ አበው ጉባየ አንድን የገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት አባል የመመረጥና የመምረጥ መብት ለተወሰነ ግዜ በቀኖና መልክ ሊያግድ ይችላል
- ማንኛውም የገዳሙ አባል ከገዳሙ ክልል ውጭ ህክምና እንደሚያስፈልገው በአጽንዖ በዓት አንቀጽ በተጠቀሰው ዝርዝር መሰረት ፈቃድ ካገኝ ገዳሙ ሙሉ የህክምና ወጪውን ይሸፍናል
- የተሰጠውን የሥራ ድርሻ ከፈጽመ በኃላ ሌላ ሥራ በመጨመር በትሩፋት መሥራት ይችላል
- የተሰጠውን የሥራ ኃላፊነት መወጣት ካልቻለ ጉዳዩን ለገዳሙ አሰተዳደር ጉባየ ኃላፊነቱን በጸሎተ ማርያም ማስወረድ ይችላል
- በእርጅና ምክንያት ቢደክም የአካል ጉዳት ቢደርስበት ቢታመም በገዳሙ በነጻ አሰፈላጊውና የሚቻለው እንክብካቤ ይደረግለታል
- በገዳሙ ክልል በሚሰጡ የትምህርት ማዕከላት ውስጥ መማርና ክርስትያናዊ ህይወትን የማይፈታተኑ የምርምር ሥራወችን የማከናወን መብት አለው። ነገር ግን ለመማርም ሆነ የምርምር ሥራወችን ለማካሄድ የአበው መማክርት አስተዳደር ጉባኤ ፈቃድ ያስፈልጋል። የአስተዳደር ጉባኤው መማርንና የምናኔ ህይወትን የማይጎዳ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድን ማበረታታት አለበት።
- ማንኛውም የገዳሙ መናኝ ጽዋሚና፤ ተሓራሚ በመሆን በጽሎት በመጠመድ በገዳሙ መኖር ይችላል። ይጠበቅበታል። ነገር ግን በዝጉሐዊ ብሕትና ለመኖር የገዳሙ ፈቃድ ያስፈልጋል። ጽዋሚ ማለት ጾመኛ ምለት ሲሆን ተሐርሚ ማለት ከሐጥያት ሥራ የራቀ ከዓለም ነገር የተከለከለ ማለት ነው። ዝጉሐዊ ማለት ራሱን ለይቶ በዓቱን ዘግቶ ወደ ዓለም ሳይወጣ የሚኖር ባሕታዊ ማለት ነው።

**ግዴታ**

- የገዳሙን መተዳደርያ ደንብ የማክበር ለማኅበረ አበውና በየደረጃው ለሚገኙ የገዳሙ ኃላፊዎች መታዘዝ አለበት
- ማንኛውም አባል ከማኅበረ መነኮሳቱ አድነት ተለይቶ በቁሪት መኖር አይችልም
- ከገዳሙ ውጭ የግል ዝምድና መመስረት አይፈቀድም
- የገዳሙ አስተዳደር ጉባየ ሳይፈቅድ በዝጉሐዊ ብሕትና (በዓት ዘግቶ በጸሎት መወሰን) መኖር አይችልም
- በዕለታዊ ግጭትም ይሁን በሥራ ምክንያት ባለመግባባት የተቀያየመ የማኅበረ መነኮሳቱ አባል የዕለት መቁነን ከመቀበሉና አቡነ ዘበሰማያት ከማድረሱ አስቀድሞ በመግባባት በይቅርታና በፍቅር ካልጨረሰ መቁነኑም ጸሎቱም ፍዳ ይሆንበታል

- በሥራዓተ አበው አኗኗር በዘር በጎሳ በቋንቋ መከፋፈል አይፈቀድም።
- የማኅበረ መነኮሳት አባል የሆነ ማንኛውንም ገዳማዊ ማንነት ስሙን እንኳን ቢሆን ለማንም ማሳወቅ አይፈቀድም።
- የገዳማውያንን ዘር ዜግነት ወይንም ሌላ ተመሳሳይ የሆኑ የማንነት ጉዳዮችን መጠየቅ ወይም ለማንም ለሌላ የማኅበረ መነኮሳት አባል አንኳን ቢሆን መናገ አይፈቀድም
- በቆዳ ቀለም በዘር በዜግነት ወይንም በሌላ ተመሳሳይ በሆኑ የማንነት ጉዳዮች ተለይቶ መሰባሰብ ሊላ ገዳማውያንን ማንነትን መሰረት ባደረገ ምክንያት ማግለል የምከረ አበው ጉባየ በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ከገዳም ያባርራል።

## 9 ማኅበረ መነኮሳትን መጎብኘትና መጠየቅ

- በእንግዶችና በገዳም ጉብኝት ዝርዝር መመርያ ገዳሙን እንግዶች እንዴት መጎብኘት እንደሚችሉ በስፋት የተገለጸ ስለሆነ ይህ አንቀጽ ማኅበረ መነኮሳትን ለመጎብኘት ስለሚመጡት አንግዶች ብቻ ይመለከታል
- የማኅበረ መነኮሳት ዝርዝር ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ካልሆነ በቀር ለሌላ ለማንም አይሰጥም
- ለማኅበረ መነኮሳት ብቻ ተለይቶ ከተከለለው ቅጽር ከማኅበረ መነኮሳትና ከሊቀ ጳጳሳት ውጭ ማንም መግባት አይፈቀድለትም።
- ከቢተ ክርስትያን የበላይ መዋቅር የሚመጣ እንግዳ እንኳን ቢሆን ጽጽስና የሌለው ከሆነ ለማኅበረ መነኮሳት ብቻ ተለይቶ ከተከለለው ቅጽር ግቢ መግባት አይፈቀድለትም። ነገር ግን ለህግ ማስከበር ሥራ ከሚመለከተው አካል ይህን የሚያረጋግጥ መረጃ ካለው በአበምኔቱ እውቅና መግባት ይችላል።
- ማንኛውም የመናኝ ቤተሰብ ዘመድ ወይም ወዳጅ በዚህ ገዳም ዘመዴ ይገኛልና ልጠይቀው መጥቻለሁ ካለ የገዳሙን ህልውና የሚፈታተን ሰው አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚጠቅሙ መሰረታዊ ጥያቄዎችን እንዲሁም ስለመናኙ ማንነትና ስም ይጠየቅና የተባለው ሰው በገዳሙ ስለመኖሩ እናጣራለን ተብሎ በእንግዶች ማረፊያ እንዲያርፍ ይደረጋል። ከዚያም የተባለው ሰው በገዳሙ ያለ ከሆነ እከሌ የሚባል ሰው ያውቅ እንደሆነ ተጠይቆ አውቀዋለሁ ካለ ሊጥይቅህ መጥቷልና ልታገኘው ትፈልጋለህ ወይ ተብሎ ይጠየቃል። አዎ አግኝቸው ስለደህንነቴ እንዲያውቅና ሰለ ሁሉም ነገር ልነግረው እፈልጋለሁ ካለ እንዲገናኙ ይደረጋል። አይ ላገኘው አልፈልግም ደህና መሆኔን ነግራችሁ ሸኙት ካለ ወይም አይ ለምናኔ ህይወቴ ፈተና ስለሚሆንብኝ ላገኘውም አልፈልግም እዚህ መኖሬንም አትንገሩት ካለ ጠያቂው በጥሩ ሁኔታ ተስተናግዶ ይሸኛል።
- ለማኅበረ መነኮሳት የግል ስጦታ ምግብ ለብስ ወይም ሌላ ስጦታ መስጠት አይፍቀድም። የአድነት ገዳም በመሆኑ ማንኛውም ስጦታ ለገዳሙ ገቢ ተደርጎ መነኮሳቱ በጋራ የሚጠቀሙበት ይሆናል።
- ከገዳሙ በረከት ለመቀበል የሚመጡ ሁሉ ከገዳሙ የሚሰጥ ልዩ ማስታወሻ በስጦታ መልክ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ ስጦታ ምንም መሆን እንዳለበት በአበው የአስተዳደር ጉባኤ የሚወሰን ሲሆን ማንኛውም አይነት ስጦታ ግን በማኅበረ መነኮሳቱ ጸሎት የተደረገበት ይሆናል።

## 10 ከገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት መውጣት

- ማንኛውም የገዳሙ መናኝ በማንኛውም ግዜ ከገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት መለየት አፈልጋለሁ ካለ በጽሁፍ ለመለየት የፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት ገልጾ ማመልከቻ ይስገባል።
- አበምኔቱ አበው የአስተዳደር ጉባኤ አባላት በተገኙበት መናኙን ያነጋግሩታል። ከማኅበረ መነኮሳቱ መለየት የፈለገው ባለመስማማት ምክንያት ከሆነ የምክረ አበው ጉባየ እንዲያነጋጋረውና ጉዳዩን እንዲከታተል ያደርጋሉ።
- መናኙ መለየት የፈገበት ምክንያት በህመም ምክንያት ከሆነ ጉዳዩን የገዳሙ ሐኪሞች እንዲከታተሉት ይደረጋል።
- መናኙ መለየት የፈለገበት ምክንያት ባለመስማማት ወይንም በህመም ምክንያት ባይሆንም አበምኔቱ አበው የአስተዳደር ጉባኤ አባላት በተገኙበት መናኙን ያነጋግሩታል። ነገር ግን በገዳሙ እንዲቆይ ወይም ሀሳቡን እንዲቀይር ምንም አይነት ጫና መፍጠር የለባቸውም።
- መናኙ የትራስፖርት ወጪ ወይም ለሌላ አስፈለጊ ጉዳይ ገንዘብ ካስፈለገው የአስተዳደር ጉባኤ ወስኖ በስጦታ መልክ የተወሰነ ገንዘብ ሊሰጠው ይችላል።ይህ ስጦታ እንጂ ህጋዊ የሆነ ግዴታ አይደለም።
- በገዳሙ በምንና ለቆዩ መነኮሳት ገብተውት የነበሩትን ሥምረት (ቃል ኪዳን) የገዳሙን ህይወት አንዲሁም ማኅበረ መነኮሳትን እያስታወሱ በሄዱበት ሁሉ በመንፋሳዊ ህይወታቸው እንዲቆዩ የሚረዳ ልዩ ማስታወሻ የሰጣቸዋል። ይህ ስጦታ ምንም መሆን እንዳለበት በአበው የአስተዳደር ጉባኤ የሚወሰን ሲሆን ማንኛውም አይነት ስጦታ ግን በማኅበረ መነኮሳቱ ጸሎት የተደረገበት ይሆናል።

- የአስተዳደር ጉባኤ ለተሾኙ መናኝ ይሾኘት ጥራዝ ያዘጋጃል። ይህ ጥራዝ ቢያንስ (ሀ) የገዳሙን ልዩ ማስታወሻ (ለ) ከገዳሙ በገንዘብ መልኩ የተሰጠውን ስጦታ (ሐ) የስንብት ደብድቤውን ይይዛል።
- የስንበት ደባድቤው ገዳሙ ከመናኙ ጋር ያለው ማንኛውም ህጋዊ ጉዳዮች መቋረጣቸውንና ተሰናባች መናኝ ከምንም አይነት የገዳሙ ዕዳዎችና ኃላፊነቶች ነጻ መሆኑን እንዲሁም ማኅበረ መነኳሳቱ ምንም ግዜም በጸሎት እንደማይረሱት ማተት ይኖርበታል።
- ተሰናባች መናኝ ከሚኖርበት ግዴታዎች አንዱ ለማንም ቢሆን የገዳሙን ማኅበረ መነኮሳት ስም ዝርዝር አለመስጠት ነው። ይህም ገና ወደ ገዳሙ ሲገባ በፊርማ ያረጋገጠው ህጋዊ ግዴታ ነው።
- ተሰናባች መናኝ የገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት ብቻ የሚለብሱትን ልብስ ያስረክባል። ገዳሙን ለቆ ሲሄድ የሚለብሰውን ልብስ ቢያንስ ከአንድ ተቀያሪ ልብስ ጋር ገዳሙ ያዘጋጃል።
- በመናኙ ስንብት አበምኔቱ ማኅበረ መነኮሳቱ እንዲገኙ ያደርጋል። ጸሎትም ይደርሳል። ተሰናባቹ መናኝ ጸሎተ ማርያምን ዝቅ ብሎ ይቀበላል። ከአበምኔቱ መስቀል ከአበው በረከትን ተቀብሎ ይሸኛል።
- ማንኛውም በገዳሙ በምንና ቆይቶ ከገዳሙ ማኅበረ መነኮሳት መለየት የሚፈልግ መነኩሴ ወይንም በአመንክሮ የነበረ መናኝ በምንም አይነት ምክንያት ከገዳሙ ሲወጣ የምንኩስና ኃላፊነት ልዘልቀው አልቻልሁም ብሎ እንኳ ቢሆን ከገዳሙ የሚሸኘው በልዩ ፍቅር በእንባና በጸሎት መሆን አለበት።

# አባሪዎች

## 1. ስምረት

- ዓለሙንና በዓለሙ ውስጥ ያለውን ፍትወት ሁሉ በእናንተ ጸሎት በእመ ብርሃን እርዳታ በቅዱስ ዮሐንስ ምልጃ በእግዚአብሔር ኃይልም እችለዋለሁ
- ንጽህናን ትሕትናን መቲረ ፈቃድን (መታዘዝን) በእናንተ ጸሎት በእመ ብርሃን እርዳታ በቅዱስ ዮሐንስ ምልጃ በእግዚአብሔር ቸርነት እጠብቃለሁ
- ከገዳሙ ከማገኘው መቁነን በቀር ከማኅበሩ የተለየ ጥሪት አላበጅም። መንኖ ጥሪትን እጠብቃለሁ። ለዚህም በእናቴ በእመ ብርሃን በእረዳቴ በቅዱስ ዮሐንስ በኃያሉ በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ
- እንደ ማኅበሩ ሕግ ይህን ሥራ ያንን አምጣ እዚህ ሂድ እዚያ ግባ ብትሉኝ በትሕትና ታዝዤ አፈጽማለሁ። ትንሺ ትልቅ ሳልል ለሁሉም እታዘዛለሁ። ለዚህም በእናቴ በእመ ብርሃን በረዳቴ በቅዱስ ዮሐንስ በኃያሉ በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ
- ማኅበረ መነኩሳት አባቶቼን እንዲሁም መናኝ ወንድሞቼን ማንኛውንም ሰው እግዚአብሔር በሰጠው የቆዳው ቀለም ጎሳው ቋንቋው ዜግነቱና ማንነቱን መሰረት አድርጌ አላቀርብም። አላርቅም። አልለያይም። ከፍ ዝቅ አላደርግም። ለዚህም በእናቴ በእመ ብርሃን በረዳቴ በቅዱስ ዮሐንስ በኃያሉ በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ
- የገዳሙን ህግ ሥርዓት ደንብና መመርያ ሁሉ በእናንተ ጸሎት በእመ ብርሃን እርዳታ በቅዱስ ዮሐንስ ምልጃ በእግዚአብሔር ቸርነት አከብራለሁ።
- ነፍሴን ለእግዚአብሔር ሥጋዮን ለማኅበር በእናንተ ጸሎት በእመ ብርሃን እርዳታ በቅዱስ ዮሐንስ ምልጃ በእግዚአብሔር ቸርነት ሰጥቻለሁ።

## 2. የማመልከቻ ቅጽ

1. ሙሉ ስም ..................................................................................
2. ዕድሜ ..................................
3. የትውልድ ቀን  ወር .................... ቀን ......................... ዓመት ................................
4. አድራሻ  Street .............................................., City ............................. State ............ Zip Code ............
5. ስልክ ቁጥር ......................................................
6. የኢሜል አድራሻ ....................................................
7. ዜግነት ..........................................
8. የፓስፖርት ቁጥር ............................ የተሰጠበት ቀን ............................ የሚጠናቀቅበት ቀን .............................
9. የመንጃ ፈቃድ ቁጥር ....................................... የሚጠናቀቅበት ቀን ............................
10. ህጋዊ የመኖርያ ፈቃድ አይነት .............................  ቁጥር ...................... የሚጠናቀቅበት ቀን .............................
11. ስመ ጥምቀት .........................................................................
12. የአበ ንስሐ አባት ..............................................................................
13. በአባልነት የተመዘገቡበት ቤተ ክርስትያን ስምና አድራሻ ...................................................................................................................
14. ማዕረገ ክህነት (ካለዎት)    ....................................... ክህነት የተቀበሉበት ቀን ................ የሰጡት ሊቀ ጳጳስ ስም .......................
15. የጤንነት ሁኔታ (የጤንነት መረጃ ቅጹን ይሙሉ)
16. የሀብት የንብረት የገቢ እና የውዝፍ ዕዳ ሁኔታ (የሀብት መግለጫና ማሳወቅያ ቅጹን ይሙሉ)
17. ገዳሙ የአመካኞችን ከወነጅል ነጻ መሆን  የውዝፍ ዕዳ ሁኔታንና  ሌሎች ተያያዝ ሁኔታወችን ልምድ ባለው ተቋም እንዲረጋገጥ ያደርጋል። ስለሆነም ይህን የማረጋገጥ ሥራ ገዳሙ እንዲፈጽም የመስማምያ ቅጹን ይሙሉ
18. በዚህ ገዳም በአበው በሕብረት (በአድነት) ለመኖር የመረጡበትን ምክንያት በመዘርዘር ይጻፉ

.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................
.......................................................................................................................................................

.............................................................................................................................................................................................................................
.............................................................................................................................................................................................................................

3. **የስምምነት ቅጽ** (to be written)

4. **የምክረ አበው ጉባየ ዝርዝር የአሠራር መመርያ** (to be written)